# COVID-19:

# ለንግድ ተቋማትና ለዝግጅቶች የሚሰጥ ኢንሹራንስ

## የንግድ ተቋማት ኢንሹራንስ መረጃ

የ Washington ግዛት የንግድ ስራ ባለቤቶች ሊከሰቱ ከሚችሉ ኪሳራዎች ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የኢንሹራንስ ሽፋን መግዛታቸው የተለመደ ነው። ኮሮናቫይረስ (COVID-19) ሲቀሰቀስ፣ የንግድ ስራ ባለቤቶች አሁን ያላቸው የኢንሹራንስ ፖሊሲ እንዲህ ዓይነት ጉዳትን የሚሸፍን ስለመሆኑ ሊጠይቁ ይችላሉ።

**ሽፋን ለማግኘት ምን እንደሚያስፈልግዎት**

እንደ COVID-19 ባሉ ተላፊፊ በሽታዎች ምክንያት በንግድ ስራ ላይ ለሚከሰቱ ጉዳቶች ሽፋን ለማግኘት፣ ለፖሊሲዎ ተጨማሪ ውል መግዛት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

ይህ ተጨማሪ ሽፋን ቀደም ሲል ያለዎት መሆኑን ለማጣራት የኢንሹራንስ ወኪልዎን ወይም የኢንሹራንስ ድርጅትዎን በቀጥታ ያነጋግሩ። ተጨማሪ ሽፋን ከሌለዎትና ለመግዛት ከፈለጉ፣ የኢንሹራንስ ወኪልዎን ወይም ኩባንያ በማነጋገር መኖሩን ያረጋግጡ።

ወረርሽኙ ከመቀስቀሱ በፊት ተጨማሪ ውል ካልገዙና ለመግዛት ከፈለጉ፣ ዋስትና ሰጪው ተጨማሪ ውሉን ሊሸጥልዎ ላይፈልግ ይችላል።

## የዝግጅት ስረዛ ኢንሹራንስ

የዝግጅት ቦታዎች አስቀድሞ ቦታ ያስያዘው ግለሰብ ወይም ድርጅት የዝግጅት ስረዛ ኢንሹራንስ እንዲኖረው ይጠይቃሉ። የተላላፊ በሽታ መቀስቀስ ሽፋን በመደበኛው የዝግጅት ስረዛ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ውስጥ አይካተትም። እንዲህ ዓይነት ኢንሹራንስ የሚሸፍነው እንደነዚህ ዓይነት የአደጋ ስጋቶችን ነው፡-

- አሉታዊ የአየር ሁኔታ
- የተፈጥሮ አደጋዎች
- የሰራተኛ አለመግባባቶች
- የሽብር ድርጊቶች
- ለመልቀቅ አለመቻል
- ሳይገኙ መቅረት

**ሽፋን ለማግኘት ምን እንደሚያስፈልግዎት**

በተላላፊ በሽታ ምክንያት አንድን ዝግጅት መሰረዝን ለመሸፈን የዝግጅት ስረዛ ኢንሹራንስ ፖሊሲዎ ላይ ተጨማሪ ውል መግዛት ይችላሉ። ዋስትና ሰጪዎ እንዲህ ዓይነት ተጨማሪ ውል የማያቀርብ ከሆነ፣ ከሌሎች ዋስትና ሰጪዎች መግዛት አለብዎት።

ወረርሽኙ ከመቀስቀሱ በፊት ተጨማሪ ውል ካልገዙና አንድን ዝግጅት ለመሰረዝ ለመግዛት ከፈለጉ፣ ዋስትና ሰጪው ለስረዛው ሽፋን ለመስጠት ሲል የፖሊሲውን ቀን ወደኋላ ማድረግ እንደማይችል ይወቁ። ዋስትና ሰጪዎች እንደዚህ ዓይነት ተጨማሪ ውልን መሸጥ ላይፈልጉም ይችላሉ።

**ማስታወሻ፡- Office of the Insurance Commissioner** (የኢንሹራንስ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት) ዋስትና ሰጪዎች የትኛውንም ዓይነት የሽፋን ወይም የፖሊሲ ተጨማሪ ውሎችን እንዲሸጡ የመጠየቅ ስልጣን የለውም።

**የኢንሹራንስ ነክ ጥያቄዎች አሉዎት?**

**www.insurance.wa.gov**

**1-800-562-6900**

OFFICE of the INSURANCE COMMISSIONER WASHINGTON STATE

facebook.com/wsoic twitter.com/WA_OIC medium.com/commissioners-eye-on-insurance